# ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1161/2011ን ለማሻሻል የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም.

## መግቢያ

መንግስት ለሕዝብ አገልግሎት ከሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች መሬትን ለመጠቀም፣ የአገሪቱ ከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉና የነዋሪዎቹም ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት፣ የኢንቨስትመንትና ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የከተማ መሬትን መልሶ ለማልማት፣ እንዲሁም በገጠር ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች መሬት አዘጋጅቶ ለማቅረብ፣ የመሬት ይዞታ እንዲለቁ ለተደረጉ ባለይዞታዎች ተገቢና ተመጣጣኝ ካሣና የተነሺ ድጋፍ ለመክፈል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎችን ለይቶ ለመወሰን፣ ካሣውን የመተመን፣ የመክፈል እና ተነሺዎችን መልሶ የማቋቋም ሥልጣንና ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት በግልጽ ለይቶ ለመወሰን በማስፈለጉ ምክንያት እነዚህን ተግባራት በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም እንዲቻል ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 1161/2011 መውጣቱ ይታወሳል፡፡ ሆኖም ግን አዋጁ ለልማት ተነሺዎች ከሚከፈለው የካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ የመሰረተ ልማት ገንቢው ተቋም ካሳ እንዲፈፅም፣ የወሰን ማስከበር ሥራዎችን እንዲያከናውን እንዲሁም መሠረተ ልማቱንም እንዲገነባ ማድረጉ አላስፈላጊ ጫና እና የጊዜ ብክነት እየፈጠረ ይገኛል፡፡

የወሰን ማስከበር ስራ ላይ የሚሳተፉት አካላት በርካታ በመሆናቸዉ የንብረት ማስነሳትና ለልማት የሚፈለገውን መሬት ከንብረት ነፃ አድርጎ ለማስረከብ የሚወሰደው ጊዜ እጅግ የተራዘመ በመሆኑ፣ ንብረት ገማቹ አካል ወረዳ/ከተማ ስራውን በባለቤትነት መንፈስ ባለመረዳት ንብረቶቹ ከሚያወጡት ዋጋ በላይ እጅግ የተጋነነ ዋጋ እንዲከፈል በርካታ ጥያቄ እየቀረበ በመሆኑ፣ የእርሻ ማሳዎቹ ከሚሰጡት ምርታማነት በላይ እጅግ የተጋነነ ምርታማነት ከአንድ ማሳ እንደሚገኝ ተደርጎ ዋጋ የሚሰላ በመሆኑ፣ ክፍያ የተራዘመባቸው ንብረቶች ጊዜን ታሳቢ አድርጎ በተቀላጠፈ መንገድ የማይነሱ በመሆኑ፣ ህገወጥ ግንባታዎች እየተበራከቱ በመምጣታቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎ በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እየተጠናቀቁ አይደለም፡፡ በዚህም የተነሳ መሰረተ ልማቱ ተገንብተው መሰጠት የሚገባቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም እንዳይሰጡ ከማድረጉም በላይ በመንግስት ወጪ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ችግር ዋና መንስኤው የወሰን ማስከበር

ሥራ ላይ የሚሳተፉ አካላት ብዙ መሆናቸውና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር አለመስራት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የመሬት ይዞታ እንዲለቀቅ  የተፈለገው አግባብ ባለው የፌዴራል መንግስቱ አካል ለሚከናወን መሠረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ በሚሆንበት ጊዜ ንብረት የመገመት፣ የመክፈል እና የማስነሳት ሥራ ሙሉ ለሙሉ ለክልል /ከተማ አስተዳደር አካላት መስጠትና የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር የሚያደርግ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ የአዋጅ ቁጥር 1161/2011 የተወሰኑ ድንጋጌዎች ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም የመሠረተ ልማት ገንቢ ተቋም በሕግ የተጣለበትን የመሠረተ ልማት ግንባታ ስራ ወጪ፣ ጥራት እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሥራውን እንዲያከናውን ለማስቻል ካሳ የመክፈል ኃላፊነትን የሚመለከተው የአዋጁ ክፍል ከመሠረተ ልማት ገንቢው ተቋም ላይ ተነስቶ  ለክልል እና የከተማ አስተዳደር አካላት ማስተላለፍ እንዲቻል ማሻሻያ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም መሠረት የአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 (ማለትም ንብረት የማስነሳትና ካሳ የመክፈል ኃላፊነትን ለመሰረተ ልማት ገቢ ተቋማት የሚሰጡት ድንጋጌዎች ተሰርዘው) ይህንን ኃላፊነት ለክልልና ለከተማ አስተዳደር አካላት እንዲሠጥ የሚያደርጉ አንቀጽ ተካቷል፡፡ የክልል እና የከተማ አስተዳደር አካላት የሚለው በህገመንግስቱ አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋሙትን ክልሎች እና የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን የሚመለከት ይሆናል። በዚህ ማሻሻያ መሰረት በፌዴራል መንግስቱ አካኝነት ለሚከናወን የመሰረተ ልማት ወይም የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ስራ መሬት ከማስለቀቅ ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን አስመልክቶ ከክልል በታች ላለ የአስተዳደር መዋቅር ክፍያውን እንዲፈጽም ኃላፊነት መስጠት የእነኚህን የአስተዳደር አካላት አቅም ከግምት የማያስገባ እና ሊፈጸም የማይችል ኃላፊነት ይሆናል። ስለሆነም የክፍያ ኃላፊነትን ለክልል እና ለከተማ አስተዳደሮች እንዲሰጥ ማደረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ሌላው በዚህ ማሻሻያ የተዳሰሰው ጉዳይ ከንብረት ካሳ፣ የልማት ተነሺ ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ፣ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቡና ጉዳት ካሳ ጋር ተያይዞ በተለይ በፍርድ ቤቶች የሚደረጉ ክርክሮችን በተመለከተ ያለው ጉዳይ ነው። በዚህም

መሰረት ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የሚደረጉ ክርክሮች በተለይ የፌዴራል መንግስቱ በሚያከናውናቸው የመሰረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፋያዎችን በተመለከተ በሚሆን ጊዜ ይህንን ስራ የሚያከናውነው የፌዴራል መንግስቱ ተቋም ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊሆን እንደሚገባው ተደንጓል። በተጨማሪም በተለይ በፍርድ ቤት ከሚደረጉ ክርክሮች ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ጊዜያዊ ትዕዛዞች ማለትም የፌዴራል መንግስት ተቋምን የባንክ ሂሳብ የማገድ ወይም ከአፈጻጸም ጋር በተያያዘ የፌዴራል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮችን ተገደው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የሚሰጡ ትዕዛዞች እና በቀጥታ ከፌዴራል መንግስት ተቋማት የባንክ ሂሳብ ክፍያ እንዲፈጸም የሚስገድዱ ትእዛዞች በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እውቅና ሳይኖራቸው ሊሰጡ እንደማይገባቸው ተካቷል።

## ❖ የአዋጅ 1161/21011 እና የማሻሻያዉ የንፅፅር ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | አዋጅ 1161/2011 | ማሻሻያ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | **አንቀፅ 9፣ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ሃላፊነት** | **አንቀፅ 9፣ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ሃላፊነት** | |
| 2 | 1/ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ለሥራው የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ አለበት፡፡ | 1/ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ለሥራው የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከአንድ ዓመት በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ አለበት፡፡ | |
| 3 | 2/ መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን | 2) መሬት ለህዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች | |

| ተ.ቁ | አዋጅ 1161/2011 | ማሻሻያ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| | ካሣ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ እንዲሸፍን ከተወሰነ ገንዘቡን ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል፡፡ | የሚከፈለው ካሳ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ በሚከተሉት አካላት ይሸፈናል፤ | |
| 4 | | ሀ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በፌዴራል መንግስት ለሚከናወን መሠረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ የልማት ስራው የሚካሄድበት የክልል፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ለባለይዞታዎች የሚከፈለውን የንብረት ካሳ፣ የልማት ተነሺ ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ፣ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቡና ጉዳት ካሳ ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ | |
| 5 | | ለ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተራ ፊደል (ሀ) ከተገለፁት ውጪ ለሆነ የህዝብ ጥቅም ከሆነ መሬቱ እንዲለቀቅ የተወሰነለት አካል የተዘረዘሩትን ካሳዎች እና የመቋቋሚያ ወጪ ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል፡፡ | |
| 6 | 3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ ለተነሺዎች | 3) የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት | |

| ተ.ቁ | አዋጅ 1161/2011 | ማሻሻያ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| | ካልተከፈለ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬት አያስለቅቅም፡፡ | የካሣ ገንዘቡ ለልማት ተነሺው ካልተከፈለ ከመሬቱ አያስለቅቀውም፡፡ | |
| | አንቀጽ 20. ስለ ይግባኝ | አንቀጽ 20. ስለ ይግባኝ | |
| | 1/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ1 መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡ | 1/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ1 መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡ | |
| | 2. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀን ውስጥ ይግባኝ ለክልል ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተሞች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ከሆነ ልማቱ እንዲይጓተት ቦታውን አስረክቦ ክርክሩን የመቀጠል መብት አለው፡፡ | 2. ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ (ሰላሳ) ቀን ውስጥ ይግባኝ ለክልል ከፍተኛው ፍርድ ቤት፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተሞች ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ከሆነ ልማቱ እንዲይጓተት ቦታውን አስረክቦ ክርክሩን የመቀጠል መብት አለው፡፡ | |
| | | 3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ /ሀ/ መሰረት የሚነሱ ማናቸውም አይነት የፍርድ ቤት ክርክሮች የሚቀርቡት የመሰረተ ልማቱን ወይም የማህበራዊ አገልግሎቱን የሚያከናውነው የፌዴራል መንግስቱ ተቋም ዋና | |

| ተ.ቁ | አዋጅ 1161/2011 | ማሻሻያ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| | | መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባለው የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። | |
| | 3/ ተነሺው ንብረቱን በማስረከቡ እና በቅሬታ ምክንያት ካሳውን ባለመውሰዱ ለይግባኙ ክርክር የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለው እና በዚህ ምክንያት የሚቸገር ከሆነ መንግስት ነፃ የህግ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ | 4/ ተነሺው ንብረቱን በማስረከቡ እና በቅሬታ ምክንያት ካሳውን ባለመውሰዱ ለይግባኙ ክርክር የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለው እና በዚህ ምክንያት የሚቸገር ከሆነ መንግስት ነፃ የህግ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ | |
| | | 5/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ /ሀ/ መሰረት የሚነሱ ማናቸውም አይነት የፍርድ ቤት ክርክሮች ተከትሎ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የመሰረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት አከናዋኙ ተቋምን የባንክ ሂሳብ የማገድ ወይም በቀጥታ ክፍያ እንዲፈጸም የሚሰጥ ትዕዛዝ በፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ትዕዛዝ አማካኝነት ብቻ ይሆናል። | |
| 7 | **አንቀፅ 23. የክልሎች፤ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ስልጣን እና ተግባር** | **አንቀፅ 23. የክልሎች፤ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ስልጣን እና ተግባር** | |
| 8 | | 5/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9(2) መሠረት መሬት እንዲለቁ ለተደረጉት ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሳ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል፤ | |

## አዋጅ ቁጥር -----/2016

## ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ 55(2)(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር------------/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

1) የአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተሰርዘው የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ተተክተዋል፣

2/ "መሬት ለህዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለው ካሳ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ በሚከተሉት አካላት ይሸፈናል፣

ሀ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በፌዴራል መንግስት ለሚከናወን መሠረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ የልማት ስራው የሚካሄድበት የክልል አስተዳደር ለባለይዞታዎች የሚከፈለውን የንብረት ካሳ፣ የልማት ተነሺ ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ፣ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቡና ጉዳት ካሳ ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

ለ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተገለፁት ውጪ ለሆነ የህዝብ ጥቅም ከሆነ መሬቱ እንዲለቀቅ የተወሰነለት አካል የተዘረዘሩትን ካሳዎች እና

የመቋቋሚያ ወጪ ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል፡፡”

3/ “የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የካሣ ገንዘቡ ለልማት ተነሺው ካልተከፈለ ከመሬቱ አያስለቅቀውም፡፡

2) የአዋጁ አንቀጽ 20 ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (3) እና (5) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (3) ንዑስ አንቀጽ (4) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

“3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የሚነሱ ማናቸውም አይነት የፍርድ ቤት ክርክሮች የሚቀርቡት የመሰረተ ልማቱን ወይም የማህበራዊ አገልግሎቱን የሚያከናውነው የፌዴራል መንግስቱ ተቋም ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባለው የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው።

5/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የሚነሱ ማናቸውም አይነት የፍርድ ቤት ክርክሮች ተከትሎ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የመሰረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት አከናዋኙ ተቋምን የባንክ ሂሳብ የማገድ ወይም በቀጥታ ክፍያ እንዲፈጸም የሚሰጥ ትዕዛዝ በፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ትዕዛዝ አማካኝነት ብቻ ይሆናል።”

3) የአዋጁ አንቀጽ 23 ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተጨምሯል፤

5/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መሬት እንዲለቁ ለተደረጉት ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሳ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል፤

## 3. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ -----------------ቀን---------/ 2016 ዓ.ም

ሣህለ ወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**Proclamation No --------/2023**

**A Proclamation to Amend Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement (Amendment) Proclamation**

**WHEREAS** it has become necessary to amend the Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement Proclamation;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(2) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. **Short Title**

   This Proclamation may be cited as the "Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement (Amendment) Proclamation No. -----/2023".

2. **Amendment**

   Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement Proclamation No. 1161/2019 is hereby amended as follows:

   1/ Sub-articles (2) and (3) of Article 9 of the Proclamation are hereby deleted and replaced by the following new Sub article (2) and (3);

   "2/ When the land is expropriated for public purpose, payment of compensation and resettlement cost is covered by the following bodies:

   a) When the land is expropriated for infrastructure and social service development to be carried out by the federal government, the regions administration where the development is carried on shall have the duty to make the payment for asset compensation, support to the displaced people, economic loss compensation, social ties

discontinuance and moral damage compensation, to the land holders;

b) When the land is expropriated for public Purpose other than what is provided under sub-article (a) of this Article, the land requiring body shall pay the required compensation and resettlement expenses to the city or woreda administration."

3/ "the city or woreda administration shall not require handing over of the land unless compensation is made to the landholder in accordance with sub-article (2) of this Article."

2/ the following new sub-articles (3) and (5) are added under article 20 of this proclamation and the existing sub-article (3) is renumbered as sub-article (4);

"3/ without prejudice to sub-article (2) of this article, any type of court litigation arising under paragraph (a) of sub-article (2) of article 9 of this proclamation shall be submitted to the federal first instance court in the place where the headquarters of the federal government institution that carries out the infrastructure or social service is located.

5/ In accordance with paragraph (a) of sub-article (2) of article 9 of this proclamation, an order to freeze the bank account or an order to make direct payment from the account of the institution of infrastructure or social services shall only be given by the order of the president of the federal first instance court."

3/ the following new sub-article (5) is added under article 23 of this proclamation;

"5/ shall pay or cause to be paid appropriate compensation to landholders who have been displaced in accordance with sub-article (2) of Article 9 of this proclamation."

3. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this ------------Day of --------, 2023

SAHELE WORK ZEWDE
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA